# ግድብ ትግልን ለመገደብ!

ሱሌይማን አብደላ

አረመኔው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሕዝብ አመጽ ይነሳብኛል ብሎ የምርቃና ዕንቅልፍ እያጣ ነው። በተለመደውና በታወቀው ማደናገሪያ ቀፍቃፊነቱ የሕዝብን ትኩረት ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመውሰድ ጊንጥ ያለበትን ድንጋይ ሳይቀር እየፈነቀለ ነው። በዚህም መሰረት የሕዝብን ትግል ለማምከን ግድብ የሚል ጉዳይን ወደ መድርክ ወርውሮ ንትርክና አታካሮ ፈጥሯል።

ቢያንስ አራት ትላልቅ ግድቦች ተሰርተዋል (ግልገል ጊቤ 1 ና 2፣ ጣና በለስ፣ ተከዜ) እያሉን፣ ዛሬም መብራት በፈረቃ ነው። ግልገል ጊቤ 3 ም በቅርቡ ያልቃል ተብሏል። ሌላ የ 80 ቢሊዮን ብር ግድብ በአሁኑ ጊዜ መገንባት ማስፈለጉ ራሱ ጥያቄዎችን ይጋብዛል። በተለይም የሚቀምሰው፣ የሚበላው ባጣው ሕዝብ ላይ ገንዘብ አውጣን የሚያስከትል ከሆነ! የወር ደሞዝ ንጥቂያና ይህንንም ሕዝብ ወዶ ከፈለ አዋጣ ማለት ዘዴን በደርግ ጊዜም ያየነው ነው። ኮሾ ብልጣ ብልጥነት። ቦንድ ግዙ ጫጫታም የባዛሩ ዓይነት ነው-- ክፈሉ በግድ። ይህን መቃወም ተገቢ ነው። ከዚህ ባሻገር ግን ወያኔ ግድቡን መገንባት አለመገንባት በሚል ሊያስነሳ እየሞከር ያለው ውዝግብ፣ ግድብን ትግል ለመገደብ ማቆሚያ የማድረግ ተንኮል ነው። ይህን የሌለ ውዝግብ ጭሮ በዚያው ደግሞ ተንኮሉን የሚቃወሙትን ሁሉ በግብጽ ነጭ ለባሽነትና በሻዕቢያ ቅጥረኛነት ለመክሰስ መችኮሉ ግቡ ምን እንደሆነ ያሳየናል። አለአቅሙም ግብጽ ላይ የከፈተው ድንፋታና በዚያውም በሻዕቢያ ላይ የጀመረው የወረራ ጩኸት የሕዝብን ዕይታ ወደ ውጭ ለማድረግ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። የውስጥ ሁኔታ ሲበሸቅጥ የውጭ ጠላት ፍለጋው ሁሌም መድራቱ የሚጠበቅ ነው። ወያኔ ህዝባዊ አመጽን ካስቆመለት ኤርትራን ከመውጋት አይመለስም።

አዲስ የአባይ ድልድይ ለመስራት ሆነ ለማሰራት ወያኔ ብቃትም ውክልናም የለውም። የመብራት ሀይል ለባዕዳን ሸጦ ሲከብርና ሀገሪቷን ሲመዘብር ይታየዋል። የቋመጠው ለዚህ ነው። ለምንስ መለስ፣ ባለቤቱና ወያኔዎች ሁሉ የዘረፉትን ብዙ

ቢሊዮን ብር መልሰው ለግድቡ መገንቢያ አያውሉትም? ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ዋናው ጉዳያችን ግድብ ግንባት ሳይሆን ሀገርን ከወያኔ ጥፋት ማዳንና ዴሞክራሲን ማስፈን ነው። በመሀል የተሸነቀረው የአባይ ግድብ ጉዳይ የወያኔ ተንኮል ነው። በደፈናው ግድብ መሰራቱን የሚቃወም የለም-- በድሀ ሕዝብ ላይ ጫንቃ ሰባሪ ጫና እስካልሆነ ድረስ። በተጨባጭ ግን ዴሞክራሲ በሌለበት ሀገር፤ የሀገር መሬት ለባዕዳን በርካሽ እየተሸጠ ባለበት ሀገር፤ መብት ታፍኖ ብዙ ሺዎች በእስር በሚሰቃዩበት ሀገር፣ በቀን እጁ የሀገር ገንዘብ ካዝና ቁልፍ ከፍቶ፣ በግራ እጁ እየሰረቀ በተለያየ መንገድ ወደ ባዕዳን ሀገሮች የሚያሸሽ በሌብነት የተካነ ወሮበላ ቡድን በሚገዛበት ሀገር፣ ዋናው ግዳጅ ይህን ጸረ ሕዝብ አገዛዝ መጣል ነው። ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው። ስለዚህም በግድቡ ዙሪያ ወያኔ ሊጭር የሚከጅለውን ጥቅመ ቢስ ውዝግብ ወደ ጎን ትቶ በዋናው ጉዳይ--ማለትም በወያኔ ላይ ሕዝባዊ አመጽን ማነሳሳት ላይ-- ማተኮር ያስፈልጋል። ወያኔ ወደ ዘረጋው ወጥመድ ገብተን ግድቡ ይጠቅማል እናዋጣ አናዋጣ ዓይነት ክርክርና ንትርክ ውስጥ መዳከር የለብንም።

በቅድሚያ ብዙ ብዙ ጥያቄዎች አሉ መልስ ልናገኝላቸው የሚገቡ። አሁን ያለው ብቻ ሳይሆን እስከ ልጅ፣ ልጅ ልጅ … ልጅ የሚደርስ ትውልድ ባለዕዳ እያደረጉ፣ በሀገራችን ስም የወያኔ ማፍያዎች ምን ያህል ተበድረዋል? ከተበደሩትስ ምን ያህሉን ወደስዊዝና ሌሎች ባንኮች አሻግረውታል? ምን ያህሉ በባዕዳን ሀገሮች፣ ቤትን፣ የንግድ ተቋማትን ጨምሮ ንብረት ለመግዛት አውለውታል? ምን ያህሉስ ለዚህ ማፍያ ቡድን አባላት፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለሎሌዎቻቸው አሽረሽ ምችው ውሏል? ግንባታ ተካሄደላቸው እየተባለ ጥፋትን ለማለባበስ ከሚወራላቸው ሥራዎችስ፣ ምን ያህሉ "የወያኔ ቤቶች ያማመሩ ናቸው፣ ይፈራርሳሉ በጣት አትንኳቸው" የሚባልላቸው ዓይነት ሥራዎች ናቸው? ባልዮው የአገዛዙን ወንበር ተፈናጦበት፣ የመብራት ስርጭት በራሽን ሆኖበት፣ ሚስትዮዋ ጄኔሬተሮች ከውጭ በማስገባት በምትቸበችብበት ሀገር፣ ብዙ ብዙ ሀፍረት የለሽ ብሄራዊ የሌብነት ወንጀል ከቤተመንግሥቱ በሚፈለፈልበት ሀገር፣ ለብሄራዊ ዕድገት ተስማሚ ፖሊሲ ሊኖር አይችልም።

ከሁሉም ከሁሉም ግን የሀገርና የሕዝብ ህልውና አደጋ ላይ መሆኑን ልንስት አይገባም። ባሳለፍናቸው ሃያ ዓመታት አገዛዙ ከደደቢት ጭኖ መጥቶ፣ በሚያራምደው ፖሊሲ በሀገራችን ኢትዮጵያዊነት እየተጥላላ፣ እየተከሰሰ፣ እየተኮነነ ነው። ዘረኝነትና መንደርተኝነት እየተበረታታ ነው። ባለሶስት ቀለማቱ ብሄራዊ ሰንደቅዓላማችን ላይ የየቋንቋ መስመር ባንድራዎች ገነው፣ በየመስመር ክልሉም መንግሥታዊ መዋቅሮች ተቋቁመው፣ ወፌ ወፌ እየተባሉ፣ ለነገ ሀገር በታኝ ተንኮል እየተዘጋጁ ነው። የትላንቶቹ ዩጎዝላቪያ፣ ሩዋንዳ፣ ሱማሌ አምባገነኖች የየራሳቸው የልማት መዝሙር ነበራቸው። ሁዋላ በአገዛዛቸው ብልሹነት ምክንያት የተቀጣጠለው የርስ በርስ መተላለቅ እሳት አጠፋው እንጅ። በዚህ ዘረኛ ቡድን ፖሊሲ እኛም ወደዚያ እየተነዳን ነው። ከአራት ኪሎ ቤተመንግሥት ምድጃ ጀምሮ፣ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ለውስጥ እየተቀጣጠለ ያለውን ይኸን ጊዜ ጠበቅ እሳት (ታይም ቦንብ) ካሁኑ ተባብረን ካላጠፋነው።

የዲሲና አካባቢው ኗሪ ኢትዮጵያዊያን የወያኔው ቡድን በቅርቡ አዘጋጅቶት የነበረውን ስብሰባ በተቃወሙበት ወቅት ይዘዋቸው ከነበሩት መፈክሮች አንዱ እንደተነበበው "ከዓባይ በፊት ዘረኝነትን መገደብ፣ ማስወገድ" አጣዳፊ ተግባራችን ሊሆን ይገባል። የኢትዮጵያ ህልውና አደጋ ላይ ወድቆ ስለዕድገት ለማሰብ የሚሆን አይደለም። ከዓባይ በፊት ዘረኝነትና ፀረ-ኢትዮጵያዊው የወያኔ አገዛዝ መወገድ አለበት። ሕዝብ የሀገሩና የሥልጣኑ ባለቤት ከሆነ፣ ህልውናችን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ከቆመ፣ ሰማይ ጠቀስ እድገትን ማቀድ፣ በወል ጥረታችንም እውን ማድረግ እንችላለን። በግድብ ሽፋን ወያኔ ትግላችንን ለመገደብ የሚያደርገውን ጥረትም እናክሽፍበት። ያዳቆነ ሰይጣን ሳይቀስፍ አይለቅም እንዲሉ፣ ዘረኛው ወያኔን ለማሶገድ ስንነሳ፣ ለሌሎች ወያኔ መሰል ዘረኞች አጃቢ በማድረግ አቅጣጫ ሊያስቱን የሚሞክሩትን ተደጓሚ አራጋቢዎችም ወግዱ ማለት ተገቢ ነው።